# ኢትዮጵያ ዝንታለሟን ከምታለቅስ ሰማንያችን ቢቀደድስ?

አምበርብር ምትኩ (ከካሊፎርኛ)

አንዳንድ የተናጠልም ይሁኑ የቡድንና የማኅበረሰብ ውሳኔዎች በፊት ለፊት ገጽታቸው ሲመለከቷቸው ሊቀበሏቸው የሚያስቸግሩ ይመስላሉ፡፡ ሌላኛውን ጎን ባለማየት ወይም ለማየት ባለመድፈርና ባለመፈለግ ብዙ ጉዳቶች ሲደርሱ ይስተዋላል፡፡ እኛን እየጎዳን ያለው ይህ ዓይነቱ ነገሮችን በተለያዩ አቅጣጫዎች ያለማየት ችግር እንደሆነ ይሰማኛል፡፡

በቅድሚያ አንድ አፈ ታሪክ ልንገራችሁ፡፡ ዱሮ ፍቺ አይታወቅም ነበር አሉ፡፡ አንድ ሰው ከሚስቱ መለየት ሲፈልግ (ክርስቲያን ከሆነ) የቁም ተዝካር ያወጣና ራሱን ይገድላል እንጂ በሕይወት እያሉ በፍቺም ሆነ በሌላ መንገድ መለያየት ብሎ ነገር የሚታሰብ አልነበረም፡፡ አንድ ቀን ታዲያ አንድ ባል ከሚስቱ ጋር መኖር ያቀለሸለሸውና ራሱን በመግደል ለመለየት ይቆርጣል፡፡ እንደ ደንቡ የቁም ተዝካር እያወጣ እንግዶቹን ፈረስ በሚያስጋልብ ዳስ ውስጥ እያስተናገደ ወዲያ ወዲህ ተፍ ተፍ ይላል፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሰውዬው የእንስሳትን ቋንቋ ይችላል - የውሻን ጭምር፡፡ ባገር ቤት ሳለሁ - ያኔ ዱሮ በደጉ ዘመን - "እገሌ እኮ የጅብ ቋንቋ ይችላል" ሲባል እሰማ ነበር - በልጅነቴ፡፡

በሚስቱ ንትርክና ንዝንዝ አሣሩን ይበላ የነበረውና በዚያም ምክንያት ሞቱን የመረጠው ቁም-ተዝካረኛው ሰውዬ ውጪ ሲወጣ የመንደሩ ውሾች በውሸኛ ቋንቋ ወሬያቸውን እየሰለቁ አጥንታቸውን ሲግጡ ይመለከታል፡፡ የሱ ውሻ ግን ተክዞና ቅዝዝ ብሎ ያየዋል፡፡ እንደሌሎቹ አጥንት መጋጡንና መቆርጠሙን ትቶ አጠገቡ ከሚገኝ የመንደር ውሻ ያንዠት ጓደኛው ጋር ወሬ ሲያወራ ይሰማዋል፡፡ ከወሬውም አንዷ ዐረፍተ ነገር ጎላ ብላ ወደ ጆሮው ጥልቅ ትላለች፡፡ ያቺ የባለቤቱን ማለፍ ማግደም ተመርኩዞና ሆነ ብሎ እየደጋገመ የሚናገራት ዐረፍተ ነገር "መፍታት ሳለ መሞት፤ መፍታት ሳለ መሞት..." የምትል ናት፡፡ ሰውዬው በውሻው አንደበት ለምን እንደዚያ እንደተባለ ገባው፡፡ እርሱን ከአጉል ልማድና ከይሉኝታ እስረኝነት በማላቀቅ ከሞት ወደ ሕይወት የሚለውጥ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት እንደሆነ አድርጎም ተረጎመው፡፡ ከዚያም ሞቱን ትቶ በፍቺ ከሚስቱ ተለያዬ፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህም ፍቺ ተጀመረ፡፡ ብታምን እመን - ባታምን ተወው፡፡

ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት ብዙ የታዘብኳቸው ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ክስተቶች አሉ፡፡ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ፣ ከመደበኛም ሆነ ከኢ-መደበኛ ትምህርት ቤቶች (የማታውም እንዳይረሳ ታዲያ!) ብዙ ነገሮችን ቀስሜያለሁ፡፡ በንባብና በማዳመጥ የገበየኋቸውን ዕውቀቶችም ቀላል ግምት አልሰጣቸውም፡፡ ምራቅ የዋጥኩ ዜጋ በመሆኔ በችኮላ የምሰጠው ፍርድም አለ ብዬ እምብዛም አልገምትም፡፡ ሰው ነኝና በነገሮች እንደምሳሳትና ለመታረም ግን ዝግጁ እንደሆንኩ ከወዲሁ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

ዳርዳርታየን ልተውና ወደገደለው ልግባ፡፡

ኢትዮጵያ ዘላለሟን እየተሰቃየች የምትገኘው በዋናነት በውጭ ጠላቶቿ መሆናው ተዘውትሮ ቢነገርም የነዚህ የውጭ ጠላቶቿ ተላላኪዎች በመሆን ከጥንት ጀምሮ ጎልውናዋን እየተፈታተኑ የሚገኙት ትግራይ ውስጥ የትግራይን ሕዝብ ደጀንና መከታ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች መሆናቸው አይካድም፡፡ እነዚህ ኃይሎች አንዴ ሲገኑ ሌላ ጊዜ አንገታቸውን ቀብረው አመቺ ጊዜ ሲጠብቁና ያንን ጊዜም ሲያገኙ ያለ የሌለ የጥፋት ተልእኳቸውን ሲፈጽሙ ይሄው ሀገራችን መቅኖ እንዳጣች አለች - በሁሉም ነገር ውራ ሆና፡፡ ይህ ሽፋፋ አካሄዳችን አንዳች መስመር ካልያዘ የዓለም መሣቂያና መሣለቂያ እንደሆን የመሬታውያን ፍጻሜ መድረሱ ነው፡፡ እነዚህ የጥፋት ኃይሎች ብለው ብለው በዚህ በሰለጠነው የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 30 ሚሊዮን የሚገመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የዘር ዕልቂት በዐዋጅ መልክ ቀርፀው ለተግባራዊነቱ ሲታገሉ ድፍን አራት ዐሥርት ዓመታትን አስቆጠሩ፡፡ አማራ ብዛት ስላለው በብዛቱ ተቋቁሟቸው እንጂ የሁለትና የሦስት ሚሊዮን ሕዝብ ላይ ያ የዘር ፍጅት ታውጆ ቢሆን ኖሮ ይሄኔ የዚያ ነገድ አንድም አባል በሕይወት ሊገኝ ባልቻለ ነበር፡፡ ዐማራው ግን በመንግሥታዊ በጀት በተደገፈ ሁኔታ በዘመቻ መልክ በመርፌ ቢያመክኑትም፣ በመርዝና በጥይት ቢረፈርፉትም፣ በገመድ እያነቁ - በጦር እየወጉና በገጀራ አንገቱን እየቆረጡ በሽለቆዎች ቢጥሉትም፣ ወንድ ወንዱን በግፍ ቢያኮላሹትም፣ መሬቱንና ሀብት ንብረቱን ቢቀሙትም፣ በሂደቱ ለበረሃና ለባህር እንስሳት ቀለብነት እየዳረጉ ለስደት ቢያጋልጡትም ... ዕድሜ ለምልዓቱ በኢትዮጵያ ሲሳሳ በሌላው ዓለም ግን እየፋፋ አሁን ድረስ አለ፡፡ የነገውን ደግሞ አንድዬ ያውቃል - ስለ ነገ ግልጽ እውነቱን መናገር ባይቸግርም ለጊዜው አስፈላጊ አይደለም፡፡

እነዚህ ከትግራይ ማኅጸን የፈለቁ እርጉማን እስካሉ ድረስ መቼም ቢሆን ኢትዮጵያ ሰላም አታገኝም፡፡ ጠላቶቿ የማይተኙላት ኢትዮጵያ በዚህ መልክ መቀጠሏ ለውድመት እንጂ ለድኅነት አይሆንም፡፡ ቀን እየጠበቀ ዘርን ከሚያጠፋ ዐውሬ ካልተለዩ አጋም ሥር እንደተወተፈ ቁልቋል ሲያለቅሱ መኖር ነው፡፡ ይህን እውነት ደህና የሚባሉት ትግሬዎች ራሳቸው እንደሚደግፉት አልጠራጠርም፡፡

በዐፄ ዮሐንስ ዘመን ምን እንደተፈጠረ እናውቃለን፤ በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ምን እንደተከሰተ እናውቃለን፡፡ ከጥንት ጀምሮ ከዚህች ግዛት የሚወጣ ኃይል ለውድመቷ እንጂ ለብልፅግናዋ ውሎ አያውቅም፡፡ በጣም ይገርመኛል፡፡ ምን ዓይነት መረገም በዚያ በኩል እንደገጠመን ሳስበው ሁሌም እንደደነቀኝ አለሁ፡፡ በክፋት የቆረበ፣ ለደግነት ያልታደለ፣ በማፍረስ ጥበብ የተካነ ትልቅ የኢጋንንት ሠራዊት በዚያ በኩል አለ፡፡

የአሁኑ ደግሞ ከሁሉም የባሰ ነው፡፡ የምናገረው ከኪሴ አውጥቼ ሳይሆን እየታዘብኩት ያለሁትን የወቅቱን የከተሞቻችንን ወሬ ነው፡፡ እነዚህ ዐይን አውጣ ወያኔዎች የሰይጣንን ያህል ክፉ ቢሆኑልን ኖሮ ዕድለኞች ነበርን፡፡ ሰይጣንና ወያኔዎች በክፋትና በዐረመኔነት እጅግ ይለያያሉ፡፡ ከጓደኞቼ ጋር የምከራከርበትን እዚህ ልንገራችሁ፡፡

ልብ አድርጉ እንግዲህ፡- ሰይጣን የሚፈልገው ነፍስን ነው፤ ወያኔዎች የሚፈልጉት ደግሞ ምድራዊ ሀብትንና የበቀል ጥማት መሸንገያቸውን የሰው ደምና አጥንት፡፡ ዲያብሎስ ነፍስህን ሲፈልግ በውዴታህ እንድትሰጠው እንጂ በግድ ሊወስዳት አያስገድድህም፤ አስገድዶ

የሚወስዳት ነፍስ ወደ ጌታዋ ወደ አንድዬ እንደምትመለስ ያውቃልና ሰይጣን የሚራመደው በአስተውሎት ነው፡፡ ለምሣሌ ሰዎችን ሶዶማውያን ሲያደርግ ወይም አመንዝራዎች እንዲሆኑለትና የመንግሥቱ ወራሽ እንዲሆኑለት ሲፈልግ ጨው እያቀመሰና እርኩስ መንፈሱን ቀስ በቀስ ወደሰውነታቸው እያሰረጸ በውዴታቸው ወደ ምህዳሩ እንዲሳቡ ያደርጋል እንጂ እንደወያኔ በመንግሥት ስም በየሸርንቁላው በሚያዘጋጃቸው ድብቅና “ህጋዊ” እስር ቤቶች ንጹሓን ዜጎችን እያስገባ ወንዶችን በወንዶች፣ ሴቶችንም በሴቶች አያስደፍርም፤ ያንንም እንደጀብድ በፊልም እየቀረጸ ለማስፈራሪያነት አይጠቀምም፡፡ ይህ ተግባር ብቸኛ የወያኔ ትግሬዎች ሰማይና ምድርን ጉድ ያሰኘ ከአጋንንትም በላይ ዕጥፍ ድርብ አጋንንትነታቸውን ያስመሰከሩበት ስም የማናገኝለት ዕኩይ ተግባር ነው፡፡ በዓለም ላይ እኮ የኛኑ ጉድ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ጨምሮ እጅግ ብዙ ጨካኞችና አምባገነኖች ነበሩ፤ አሁንም አሉ፡፡ ሙሶሊኒና ሂትለር የወያኔን ሩብ ያህል አልጨከኑም - መግረፍና ማሰቃየት ማንም ያደርገዋል፤ መግደል ማንም ይገድላል፡፡ እነቢስማርክም፣ እነቦካሣም፣ እነስታሊንም፣ እነሣዳምም፣ እነጋዳፊም፣ … ገድለዋል - አሰቃይተውማል፡፡ ግን ሲያሰቃዩም ሆነ ሲገድሉ ለከት ነበራቸው፡፡ ሌሎች ጨካኞች “ሆ! ‹እንዲህ› ማድረግም እኮ ይችሉ ነበር፤ አይተው ምረውሃል እንዲያውም ወንድሜ” የሚያስብል የተወሰነ የጭካኔ ጫፎችን ይተዋሉ - አገዳደልም ወግ አለው - በርህራሄ መግደልም ያለና የነበረ ነው፤ ጣቶችን ከመቆራረጥ ጀምሮ በሂደት መግደልና በጥይት በአንዴ መግደል ለየቅል ናቸው - ስለዚህ አገዳደልም በቅጡ ሲሆን ለሟችም ለገዳይም ደግ ነው፡፡ ወያኔ ግን የሚተውልህ አንድም የጭካኔ ጫፍ የለም፡፡ የምናውቀውን ብቻ ሣይሆን በፍጹም የማናውቀውንና ሰምተነውም የማናውቀውን የጭካኔ ዘር በሙሉ እስከጥጉ በመጠቀሙ ወያኔ ለወደፊቷ ዓለም አዲስ የአጨካከን ክብረ ወሰን ባለቤት ሆኗል ማለት እንችላለን - ይህን ማይማዊ የዐውሬነት ጠባዩን “Guinness Book of Records” ቢመዘግብለት ጥሩ ነው፡፡ እናም የወያኔዎች የስቃይ ጣሪያና ወለል ከማንም ይለያል፡፡ ከነዚህ ሰዎች ጋር በአንድ መንግሥት አይደለም በጉርብትና መኖር ራሱም መረገምን ተቀብሎ ዐይንን በመጨፈን የሚኖርበት እንጂ ማዶ ለማዶ እየተያዩም መኖር የማያስችልና ሊያስቡትም የሚከብድ ተግባር ነው፡፡

ወያኔዎች 70ና 80 ዓመታትን በቅጡ ለማይኖርባት ምድራዊ ሕይወት የትም ባልታዬ ስግብግብነት ታውረው በብዙ ሚሊዮኖችና ቢሊዮኖች የሚገመት ብርና ዶላር ማካበታቸው የሰዎቹን ጅብነትና ዓሣማነት እንዲሁም በንዋይ ፍቅር መታወር ከማመልከቱ ውጪ ከሠሩት ኢሰብኣዊ ድርጊት አኳያ ብዙም አያስነውራቸውም፡፡ በህጋዊ እስረኞች ላይ ያደረጉት አስጸያፊ ተግባር ግን እነዚህ ሰዎች ጋር ሌላው እንዳይኖር በር የሚዘጋ ነው፡፡ ከነሱ መሀል አሥር ሰው፣ ሃያ ሰው፣ ሠላሣ ሰው ጨካኝና ሆዳም ሆኖ ሌላው ደህና ሰው ቢሆን ትቻቻላለህ፡፡ ዘለቃውን አንድ ሆነው ይህን ያህል የጥፋት ዘመቻ ማካሄድ ግን የተለዬ ትኩረትና ብዙ ማሰብን የሚጠይቅ ነው - እነዚህ “ሰዎች” ሰው ስለመሆናቸው አስተማማኝ መረጃና ማስረጃ ለማግኘት ራሱ ጥናት የሚያስፈልገው ይመስለኛል፤ በመንጋ ማሰብ፣ በመንጋ መወሰን፣ በመንጋ መጨከን፣ በመንጋ እምብርት ማጣት፣ በመንጋ ሆኖ እነሱ የተናገሩትን፣ የሆኑትንና ያደረጉትን ሁሉ መናገር፣ መሆንና ማድረግ ምናልባት በተወሰነ መልኩ ከአንበጣና ከዱር ግሪሣ ጋር ይመሳሰል እንደሆነ እንጂ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር ብዙም አይቀራረብም - ደግሞም የተማረውም ያልተማረውም አንድ ሲሆንና መንጋነት የኅሊናን ጤናማነት ሲያቃውስ ስታዩ እንደሰው ያስጨንቃል፡፡ የሰይን ጆሮ ይደፈንና እነሱን ሳስብ ሰው መሆኔ ያስጠላኛል - አንዳንዴ እንዲያውም ራስህን አጥፋ አጥፋ የሚል መጥፎ ስሜትም የሚጠናወተኝ ጊዜ አለ፡፡ መርዘኛ ሰዎች በተጎዱ ሰዎች እግር ራሳችሁን ተኩና እናንተ ውድ አንባቢያንም ይህን የነሱን የክፋት ክምር በጥሞና አስቡት፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ካህናት አናደዋቸው ሳለ “አንድሽ አንባቢ፣ አንድሽ ተርጓሚ ሆነሽ መንግሥቴን ትበጠብጫለሽ” እንዳሉና የመሰላቸውን ፍርድ እንደፈረዱባቸው በታሪክ ድርሳናት አንብበናል፡፡ እነዚህ ወያኔዎችም አንዱ ንግዱን፣ ሌላኛቸው ፖለቲካውን፣ አንዱ እስር ቤቱን፣ ሌላው ዲፕሎማሲውን፣ አንዱ ማዕደኑን፣ ሌላው ፋብሪካውን፣ አንዱ ኮንዶምንየሙን ሌላው የመሬት ችብቸባውን፣ አንዱ ግድያውን ሌላው ግርፊያውን፣ አንዱ ግብርናውን ሌላው ሙስናውን፣ አንዱ ፖሊስነቱን፣ ሌላው መከላከያውን፣ አንዱ ደኅንነቱን ሌላው ሚሊሻውንና ልዩ ኃይሉን፣ አንዱ “ፌዴራል” መንግሥቱን ሌላው የክልል “መንግሥታት”ን፣ አንዱ ወንዶችን እየደፈሩ ቅስምን መስበሩን፣ ሌላው ወፌላላውንና ብልት ላይ ኮዳ እያሰረ ማኮላሸቱን፣ አንዱ ንብረት ማሸሹን ሌላው የሸሸ ንብረት ተቀብሎ መሸጡን፣ … ይህን መሰል የጥፋትና ውድመት ኃላፊነቱን ሁሉ በዝግ ስብሰባቸው ተከፋፍለው መላ ሀገራችንንና ሕዝቧን ለ27 ዓመታት ቁም ስቅላቸውን ሲያሳዩ ቆዩ፡፡ አሁን ታዲያ አይበቃቸውም? እኛስ ስቃይና መከራ በሐኪም ታዘልናልን? የኛ ዝምታና ቻይነት ለዚህ መሰሉ መዘባነንና ከሰውነት ተራ መውጣት እንደዳረጋቸውስ አስበነው እናውቃለን? የነሱንም ዕዳ ከማብዛት፣ የኛንም ፍዳ ከመከመር ሁለታችንም ነፃ የምንወጣበትን መንገድ እንፈልግ፡፡

አሁን ለኔ የሚታየኝ ብቸኛው አማራጭ ከዚህ ስቃይ ለመውጣት እነሱን መርሳት ነው፡፡ እነሱን ለመርሳት ደግሞ በቀድሞዋ ትግራይ ልክ የራሳቸውን መንግሥት መሥርተው እንዲኖሩ እነሱን መለመን ነው፡፡ አሁን እንደምናየው በዕቅዳቸው መሠረት በ30 እና 40 ዓመታት ውስጥ ካለገልማጭና ካለቆንጣጭ ከመላዋ ኢትዮጵያ በተዘረፈ ሀብትና ንብረት ትግራይ አውሮፓን የምታስንቅ የኢንዱስትሪ መንደር ሆናለች፡፡ የኔ አጎትና አክስት ዳፍንት ውስጥ እየተጨናበሱ ወደ ትግራይ የሚሄደውን የከባድ ሾልት ምሰሶ በየተራ እየጠበቁ ሲያድሩ የትግራይ ገበሬ በሙብራት፣ በስልክና በንጹሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ብዙም ሳይቸገር ይኖራል - ዕድመ ንሰውዓት ጀጋኑ! ዛሬና አሁን በተፈጠረላቸው ዕድል ጠባቂና ባለቤት ከሌላት ኢትዮጵያ እንደዐይጥና ፍልፈል ሌት ከቀን ያጓጓዙትና በየሥርቻው ያከማቹት ነገር የሚያልቅባቸው ከሆነና ከኛ የሚፈልጉት ነገር ካለ እነሱን ሳናይ በሌላ አካል በኩል ልናቀብላቸው የሚያስችለን መንገድ ተፈልጎ ለቀጣዮቹ መቶና ሁለት መቶ ዓመታት ስማቸውንም ሳይቀር የማንሰማበት ሁኔታ ቢፈጠር በበኩሌ ደስ ይለኛል፡፡ የፈጠሩት psychological trauma እንዲህ በቀላሉ የሚደበዝዝም ሆነ የሚጠፋ አይደለም - ሃደ ጥዑይ ትግራዋይ አነ ዝስምዓኒን ህርቅ ዘብል ስምዒት ከመይ ገይሩ ምርዳዕ ዝክል አይፈልጥን - ቁስለኛና አቁሳይ ወይም የአቁሳይ ወገን ብዙውን ጊዜ በስሜት አይግባቡም፡፡ እንደ እውነቱ የዘረፉት ሀብትና ንብረት አይሰማኝም፡፡ እንደተባለውና እንደሚባለው “ትግራይ እስክትሰምጥ” ከመሀል አገር እየወሰዱ ያከማቹት ገንዘብም ሆነ ሌላ ንብረት ምንም ማለት አይደለም - ከፍ ሲል እንደጠቆምኩት ገብጋባነታቸውንና ይሉኝታቢስነታቸውን ከማሳየት በስተቀር፡፡ ከነሱ ነፃ የምንወጣበት ዕድል ከተፈጠርልን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሠርተን እናገኘዋለን፡፡ ብቻ እነሱ ራሳቸውን እንዲችሉልንና እንደመዥገር ከተጣበቁብን የከሳ ሰውነታችን እንዲላቀቁን በሚያመልኩት አለቃቸው በሊቀ ሣጥናኤል እንለምናቸው፡፡ የወሰዱትን የሀገር ሀብትም እዚያው ይቋቋሙበት፤ ባፍንጫችን ይውጣ፡፡ ብቻ ይገላገሉን - እንገላገላቸው፡፡ የአየር ኃይሉንም ሆነ የአየር መንገዱን ንብረት እንደወሰዱት ሁሉ በዚያው ይቅር፡፡ ሀብት ይጠፋል፤ ይገኛል፡፡ በሥነ ልቦናችንና

በአካላችን ያደረሱት ጥፋትና የኅሊና ጠባሳ ግን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ሲጠዘጥዘን የሚኖር ነውና በኅያው እግዚአብሔር ይሁንባችሁ ትግራይ ከቀረው የኢትዮጵያ ግዛት ተገንጥላ ራሷን  እንድትችል ታቦት አውጥተንና ተንበርክከንም ቢሆን እንለምናት፤ ወያኔዎችንም በፆም በጸሎት ታግዘን እንለምናቸው፡፡ ለዚህም ፈጣሪያችን ይርዳን - አንጀታቸው ራርቶ በቶሎ እንዲለዩን - እውነቴን ነው፡፡ ሰማንያችን ካልተቀደደ ሰውነታችን እንደተቀደደና እንደተዋረድን እስከወዲያኛው መኖራችን ነው፡፡ ከነሱ ጋር መኖር ደግሞ ፍርድ የሌለው የጨለማ ኑሮ መሆኑን ከተረዳሁ ቆይቻለሁ፡፡ ለዘመናት አብሮ ሲላቀስ የነበረ ሕዝብ ሲለያይ በየትኛውም ወገን ጥሩ ስሜት አይርም፡፡ ግን ደግሞ “ከሁልጊዜ ፈስ የአንድ ቀን ምንትስ” እንደሚባለው  ልጆቻችንን ገድለው ለማይረኩና ሀብት ንብረታችንን በልተው ለማይጠረቁ ጭራቆች እየገበርን ዘላለማችንን ማቅ ከምንለብስ ተለያይተን ብናየው መልካም ይመስለኛል፡፡ ውድ አንባቢስ ምን ትላለህ?